# በግዜር እየማሉ?

ምን ተማሩ ዶ/ር—ዶ/ር ፕሮፌሰር?
ሙሉ ጎልማሳ እድሜ ምንስ አስተማሩ?
    ብቅ እልም እያሉ
    እርቅ ሽምግልና "ባህላችን" እያሉ
    በግዜሩ እየማሉ
    ህዝብ ያዘናጋሉ?
    የጦቢያን ስቃይ ምነው ያረዝማሉ?

ይተዋት ብርቱየን
የኔን ጦቢያየን
እሷን ለቀቅ ያርጓት
    እጅ እግሯን ሰንሰለት
    ደረቷን ለጥይት…
    ለህሊና ኖሮ ለህሊና መሞት…

ምን ተማሩ ዶ/ር—ዶ/ር ፕሮፌሰር?
ሙሉ ጎልማሳ እድሜ ምንስ አስተማሩ?

    ሞራላዊ እሴትን ምንም አልተማሩ?
    ከብርቱ … ይማሩ
ምን ሲማሩ ኖረው፣ ምን ምን አስተማሩ?
    ደሞ "የተማሩ"
    ቀድሞ መች ተማሩ… እንዲያ እንደ መልህቁ…

"መልህቅ በባህር ውስጥ ብዙ አመት በኖረ
ተዘፈዘፈ እንጂ መች ዋና ተማረ"

አሌክስ ቱሉ
alextulu@gmail.com